

# የገነት ምስጢር

## (The Mystery of Paradise)

**በጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ (Bishop Earthquake Kelly)**


በማኒፌስት (Manifest) ላይ በፔሪ ስቶን ጁኒየር (Perry Stone jr.) የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ፔሪ ስቶን ጁኒየር በማኒፌስት ላይ



--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር -----------------------------

ያንተ ወይም ደግሞ ልጅ የሞተበት አንተ የምታውቀው ሰው ፥ ህፃን ሊሆን ይችላል ወይም የ8፣ የ9፣ የ10 አመት ልጅ ወይም ደግሞ ከጌታ ጋር ለመሆን የሄደ ወጣት ይኖር ይሆን? በአሁኗ ጊዜ የት ነው ያሉት? ምን እያደረጉ ነው? ምን እየተከናወነ ነው? ተሰንጸው የተጨናገፉ ህፃናትስ? የህፃን ልጅ ነፍስና መንፈሱስ አለ? ወይስ አንዳንድ ሰዎች እንደሚያስተምሩት ልጅ እስከሚሆን ድረስ የአካል ቁርጥራጭ ጓል ነው? ዛሬ በማኒፌስት ላይ ባጣም ልዩ እንግዳ አለኝ። ከሞት በኋላ ህይወት ላይ ተከታታይ ዝግጅት እየሰራን እንገኛለን፤ ተከታታይ ዝግጅቱም በግላቸው ከሞት በኋላ ህይወትን የቀመሱና ገነትን የተመለከቱ ሰዎችን ያካተተ ነው። ከሰውነት አካላቸው ተለይተው በእውን ገነትን አይተዋል። ዛሬ ከኔ ጋር ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ከርቲስ ኬሊ (Bishop Earthquake Curtis Kelley) ይገኛል። ኧርዝኩኤክ ተብሎ የተጠራው ቦክሰኛ ስለነበረ ነው። ይህን ሰው ብትመለከቱት ቦክስ እንደሚችል ያስታውቃል። በኔ በኩል (የኔ ደጋፊ) በመሆኑ ደስ ብሎኛል። ጳጳስ፥ ድሀ ህዝቦችን መመገብን ለብዙ ዓመታት ስታከናውን ነበር፥ በመሃል ከተማ ያሉ ዕጽ አዘዋዋሪዎች፣ የዕጽ ሱሰኞች፣ ሴተኛ አዳሪዎችን ጨምሮ፤ በተጨማሪም ከድሃም ድሃና ከምስኪንም ምስኪን ለሆኑት አገልግለሃል።



ዕድሜው 24 የሆነ ወንድ ልጅ ነበረህ እናም በዩ.ኤስ. (U.S.) በውንብድና በጣም አስቸጋሪ አካባቢ በመባል በዓለም ከሚታወቁት አንዱ በሆነው በዋትስ ቀጠና (Watts District) ህዝብን በመመገብ ላይ ነበርህ። እናም የልጅህ መኪና ተጠለፈና (ታገተና) ሁለት ጊዜ ደረቱ ላይ በሽጉጥ ተመቶ በታህስስ 7, 1998 (እ.ኤ.አ) ወዲያውኑ ተገሏል።

በሀዘን ላይ እያለህ ቢሆንም ግን አንተ ራስህ በአዕምሮ አኑኢሪዝም (brain aneurysm) በሽታ መኖር የምትችል እስከማይመስላቸው ድረስ ታመህ ነበር። ይህ የሆነው በታህሳስ 2004 (እ.ኤ.አ) ነበር። ወደ ሐኪም ቤት ተወስደህ ነበር። ስለህመሙና ስለስቃዩ ለእኔ ገልጸህልኛል። ያጋጠመህን ነገር እስኪ ንገረን። ሰዎች ይህን መስማት አለባቸው።

----------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ ---------------------------

ሐኪም ቤት ስደርስ ቀጥታ ወደ መመርመሪያው ክፍል አስገቡኝ። የአዕምሮ አኑኢሪዝም እንዳለብኝ አላውቅም ነበር። ዝም ብሎ ራስ ምታት ይመስለኝ ነበር። የሆነ መድኅኒት ሰጥተውኝ ነበር ነገር ግን አልሠራም እናም ትክክል ያልሆነ ነገር ተፈጠረ። ከሰውነቴ ውስጥ አየር ገፍቶ እንዲወጣ አስገደደኝ። ልክ እንደ ልብ ድካም ደረቴ የሚጨፈለቅ ዓይነት ስሜት ተሰማኝ። ስለዚህ መተንፈስ አልቻልኩም ነበር እናም ለመተንፈስ ብቻ ስታገል ነበር። ሐኪሙና ባለቤቴ እኔን ለመርዳት እየጣሩ እንደነበር አስተዋልኩኝ ነገር ግን መንቀጥቀጥ ጀመርኩኝ።

በዚህ ጊዜ ሁሉም አየር ከሰውነቴ ወጥቶ ነበር። ወደ ሞት መሄድ ጀመርኩኝ፥ እራሴን ወደ አሰቃቂ ጉድጓድ እየሄድኩ እንዳለሁ ተመለከትሁኝ። እኔ አገልጋይ (ቄስ) ነኝ፥ ይሄ እየተከሰተ መሆን አልነበረበትም። ወደዚህ ጉድጓድ በመሄድ ላይ እያለሁ፥ አቤቱታ በማቅረብና በመጮኽ ላይ ነበርኩኝ፥ *"እግዚአብሔር፥ እንዴት እኔ ላይ ይሄ ሊከሰት ይችላል? እኔኮ የእግዚአብሔር ሰው ነኝ፥ አንተን አገለገልኩህ፣ አድርግ ያልከኝን ነገር ሁሉ አድርጌያለሁ።"* ወደ ታች በመውረድ ላይ እያለሁ ብዙ ሰቆቃና ጩኸት መስማት ችዬ ነበር። የሆነ ቦታ ላይ ስደርስ ቆምኩኝ። ከዚያም እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ሰማሁት፥ ***"በዓለም ዙሪያ በሐኪም ቤት የሚሞቱ እኔ የሌለኋቸው ሰዎች ምን እንደሚገጥማቸው እንድትሰማና እንድታይ እፈልጋለሁ።"*** በመቅበዝበዝ ይሞታሉ። እናም ይሄ ነው የሚደርስባቸው። ***"አትፍራ፥ እኔን ለማያውቁኝ ተመልሰህ ሄደህ ማስጠንቀቂያ እንድትሆን ነው።"*** አለኝ።

ከዚያም ወደ ኋላ መመለስ ጀመርኩኝ፥ ወደ አካሌም መልሶ አስገባኝ። ሐኪሞቹ እኔ ላይ ሲሠሩ፥ እንድተነፍስ ሲጥሩ መስማት እችል ነበር። ሐኪሞቹና ረዳቶቻቸው የሚያወሩትን ነገር በጠቅላላ መስማት እችል ነበር። በመደጋገም *"እዚህ ነኝ፥ እዚህ ነኝ፥ በሕይወት አለሁ፥ እዚህ ነኝ!"* ስል ነበር። በእኔ ላይ አሁንም፥ በድጋሚ አሁንም ሲሠሩ ቆዩ ነገር ግን ከቆይታ በኋላ በቃ አቆሙ። እንዲህ ሲሉ እሰማቸው ነበር፥ *"ከዚህ በላይ ማድረግ የምንችለው ነገር የለም።"* መንፈሴ *"እኔ በሕይወት አለሁ"* እያለ ነበር ነገር ግን አይኔን መግለጥም ሆነ ጣቴን ማንቀሳቀስ አልቻልኩም። አንዷን ጣቴን ለማንቀሳቀስ እየሞከርኩ ነበር ነገር ግን ሊሆን አልቻለም። *"እኔ በሕይወት አለሁ"* እያልኩኝ ነበር ነገር ግን መሳርያዎቻቸውን ማጠፋፋት ሲጀማምሩ ይሰማኝ ነበር፥ ምክንያቱም ተስፋ ቆርጠዋል።

ነገር ግን የእግዚአብሔርን ድምጽ፥ ***"ዓይንህን ግለጥ"*** ሲል ሰማሁት። ልክ ዓይኖቼን ስከፍት፥ አንድ ሴት ሐኪም ነበረች *"እንኳን በደህና ተመለስክ፣ ያመለጥከን መስሎን ነበር"* ያለችኝ። ከነበርኩበት ስፍራ ወደ ሌላ ክፍል በፍጥነት ተወሰድኩኝና የተለያዩ ቱቦዎችንና ሌሎችንም ነገሮች በታላቅ ጥንቃቄ እላዬ ላይ አደረጓቸው።

---------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር -------------------------------

ከቀናቶች በኋላ በክፍልህ ውስጥ ምን እንደተፈጠረ እስኪ አጫውተን።

----------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ ---------------------------

በታላቅ ሕመም ውስጥ የነበርኩ ቢሆንም እግዚአብሔርን በክፍሌ ውስጥ እያመሰገንኩኝ ነበር። በሁለት ትላልቅ የበረዶ ከረጢት ጭንቅላቴን መደገፍ ነበረባቸው። የደም ግፊቴ ከሚገባው በላይ ከፍ ብሎ ነበር። ሞቼ እንደሆነ ለማየት በየ 15 ደቂቃው እየመጡ ማረጋገጥ ነበረባቸው። ስለዚህ ያለማቋረጥ ያዩኝ ነበር።

አንድ የሐኪም ረዳት ወደ ውስጥ ገባች፥ እናም እኔ፤ *"ጥሩ ወደሆነ የክርስትያን ጣቢያ ትቀይሪልኛለሽ፣ ሁሉም የሚተኳኮሱበትን የፖሊሶችን ትዕይንት ማየት አልፈልግም።"* አልኳት። እሷም ጣቢያውን ለመፈለግ ሞከረች ነገር ግን አንድም ማግኘት አልቻለችም። ስለዚህ እኔም *"በቃ መብራቱን አጥፊልኝና በሩን ዝጊው"* አልኳት።

ክፍሉን ለቃ በሩን ስትዘጋው፤ ትልቅ ወርቃማ የሚያምር ነገር ወደ ክፍሉ ሲገባ አየሁ። ነገሩን ቀጥታ እያየሁት ነበር። በአልጋው ግርጌ በኩል ተቀመጠ።

ወደኋላ አስረውኝ ስለነበር መንቀሳቀስ አልቻልኩም። ቀና ብዬ ተቀመጥኩኝና *"ይሄ ነገር በጣም ነበር የሚያምረው። ምንድን ነው?"* አልኩኝ። ከዚያም ወዲያውኑ ከአልጋዬ ላይ ወደ ላይ አነሳኝ።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ------------------------------

ልክ ጳውሎስ በሁለተኛ ቆሮንቶስ እንደሚናገረው ነፍስህ ከአካልህ ውስጥ የወጣ ይመስልሃል?

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

አዎን፥ ቅርፊቴን (ስጋዊ አካሌን) ትቼው ነው የሄድኩት። አካሌን ወደ ታች እየተመለከትኩት ነበር ነገር ግን ላውቀው አልቻልኩም ነበር፤ እንደውም *"ያ ሰውዬ በመጥፎ ሁኔታ ላይ ነው ያለው፤ አይተርፍም።"* አልኩኝ። በትክክል እራሴን ነበር እየተመለከትኩ የነበረው።

ከሰኮንድ በኋላ በዛ ትልቅ ወርቃማ በሆነው ነገር ወደዚህ ወደሚያምር አትክልት ስፍራ ተወሰድኩኝ። ዙርያውን ለመክበብ የ10 ሰዎች እጅ ለእጅ መያያዝን የሚጠይቁ በጣም ግዙፍ ዛፎችን ተመለከትኩኝ። እያንዳንዱ ቅጠል ላይ አልማዝ፣ የከበረ የድንጋይ ፈርጥና በውስጡ ብሩህ አረንጓዴ የከበረ ድንጋይ ያለበት የሳር ቅጠሎችን አየሁ። ከማናቸውም የጎልፍ (golf) መጫወቻ ሜዳዎች የበለጠ በጣም የተስተካከለ ነበር።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ------------------------------

በእላዩ ላይ ተራመድክበት እንዴ?

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

የእኔ ቁመት 6 ጫማ ከ 5 ኢንች ነው፥ መልአኩ ደግሞ 7 ጫማ ነው፥ እናም መልአኩ *"ሂድ ተራመድ"* አለኝ። የከበረ ድንጋይ ያለበት ሳርም በእግሬ ውስጥ ገብቶ የሚቆርጠኝ መስሎኝ ነበር። ነገር ግን መልአኩ *"አይደለም ሂድ"* አለኝ። ስራመድበት ልክ እንደ ጥጥ ይለሰልስ ነበር።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ------------------------------

ይደንቃል! የህይወት ወንዝንም እንደተመለከትክ ተናግረህ ነበር።

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

አዎን መራመዴን ስቀጥል፥ የሆነ ወንዝ አየሁ። ወንዙ ሙዚቃ እየሰማ የሚደንስ ነበር የሚመስለው።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ------------------------------

ሙዚቃ መስማት ትችል ነበር?

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

አዎን ሙዚቃ መስማት እችል ነበር።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ------------------------------

ስለዚህ ውሃው ከሙዚቃው ጋር ነበር የሚፈሰው። ምንድን ነበር የሚመስለው?

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

ፈሳሽ አልማዝ ነበር የሚመስለው፥ እንደ ቀለጠ አልማዝ፥ ልክ የተለያዩ የቀስተ ደመና ቀለሞች ያሉት። እጅግ በጣም ተደሰትኩኝ፥ በኪሴ ትንሽ ለማስቀመጥ ፈለኩኝ። ትንሽ ለመጎንጨት ፈለኩ፥ ለመዋኘት ፈለኩ። በተፈጥሮዬ መዋኘት አልችልም ግን እዛ የመዋኘት ስሜት ተሰማኝ። ይህን በማየቴ በጣም ተደሰትኩ እናም *"ሁሉም ሰው ይሄን ማየት አለበት"* ስል አሰብኩ።

ወንዙ ከዚህ ትልቅ የሚያምር ህንፃ ውስጥ እንደሚመጣ ማየት እችል ነበር። መላእክቶችም ሲዘምሩ መስማት እችል ነበር። ከዛም ከወንዙ ባሻገር ተመለከትኩ እናም ልጄን አየሁት።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር -----------------------------

የተገደለውን ልጅህን ማለት ነው፥ አልተቀየረም?

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

በጣም የሚያምር ሆኗል። እኔም *“ሄይ፥ ስካት (scott)”* ብዬ ጮኽኩኝ። እርሱም *“አባዬ፥ አባዬ”* አለኝ። *“አንተ ነህ”* አልኩት። እርሱም *“አዎ አባዬ፥ ይሄ ቦታ አንተ ወይም እናቴ ከነገራችሁኝ የበለጠ በጣም ቆንጆ ነው።”* ብሎ መለሰልኝ። እኔም *“ስካት፥ በአንተ በኩል ከአንተ ጋር መሆን እችላለሁ?”* አልኩት። እርሱም *“አይሆንም አባዬ፥ አሁን አትችልም፥ መመለስ አለብህ”* አለኝ። እኔም *“አይሆንም፥ ጀልባው የት ነው ያለው? እዚህ ጀልባ መኖር አለበት።”* አልኩት።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር -----------------------------

ከወንዙ ባሻገር እሱ ወዳለበት ቦታ መሻገር ስለፈለክ ነው?

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

አዎን፥ እርሱን ማቀፍ ስለፈለኩ ነበር። በ1998 (እ.ኤ.አ.) ነበር ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት፥ 6 አመት አልፎታል እናም በጣም ላቅፈው ፈለኩኝ።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር -----------------------------

ስለዚህ 6 አመት አልፎታል። እናም ብዙም አልተቀየረም ግን ቆንጆ ሆኗል ብለሃል። እናም አንተን በስምህ ነው ያወቀህ፥ አባቱ እንደሆንክ ያውቅ ነበር። ሌላ ነገር ነግሮህ ነበር?

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

አዎን፥ *“አባቴ ያን ለእኔ ቃል የገባህልኝን ነገር አስታውስ”* አለኝ።

ቦክሰኛ ነበርኩ እናም እርሱ እኔን መምታት አይችልም ነበር፥ ለስላሳ ነበርኩኝ እናም ሁል ጊዜ ቀለል አድርጌ ነካ ነካ አደርገው ነበር። እኔን ማግኘት አይችልም ነበር። በማዕድ ቤት ውስጥ እየተቧቀስን ነበር እናም አቆመና በጣም ጥብቅ አድርጎ አቀፈኝ። ይሄ የሆነው ከሞትንበት ቀን በፊት ነው። እሱም *“አባቴ፥ ቃል እንድትገባልኝ እፈልጋለሁ።”* አለኝ። በጣም ጨምቆኝ ስለነበር መተንፈስ አቅቶኝ ነበር። እኔም *“ችግሩ ምንድን ነው፥ በመስሪያ ቤት የተፈጠረ ነገር አለ እንዴ?”* አልኩት። እርሱም *“አይደለም፥ ቃል እንድትገባልኝ የምፈልገው ነገር መቼም ቢሆን አንተና እናቴ ስለመዳን መስበክ እንደማታቆሙ፥ የዕጽ ሱሰኞችንና የወንበዴ አባሎችን መርዳት እንደማታቆሙ ቃል እንድትገባልኝ ነው። ይሄን ቃል የማትገባልኝ ከሆነ አልለቅህም።”* አለኝ። እኔም *“እሺ፣ እሺ፣ እሺ ልጄ።”* አልኩት። ከዛም ለቀቀኝ፥ እኔም *“አህ፥ አንተ ደህና ነህ?”* አልኩት። እርሱም *“እኔ ደህና ነኝ።”* አለኝ።

በቀጣዩ ቀን በኔቫዳ (Nevada) ስለመነቃቃት (ሪቫይቫል ተሃድሶ) ልሰብክ ወጣሁ። በህይወትህ ሊያጋጥምህ ከሚችል መጥፎው (የሚያስጠላ) የስልክ ጥሪ ደረሰኝ፥ ባለቤቴ መኪናው እንደተጠለፈና ሁለት ጊዜ በቀጥታ ደረቱ ላይ እንደተተኮሰበት ነገረችኝ። እርሱን በገነት ማየቴ፥ ለመናገር ቃላት ያጥረኛል። *“እርሱን መቀጠል አለብህ። ወደዚህ መምጣት አትችልም ምክንያቱም አልጨረስህም፥ መጨረስ አለብህ። እንደምትጨርስ ቃልህን ሰጥተኸኝ ነበረ። ተመልሰህ ሄደህ መጨረስ አለብህ።”* ብሎ አለኝ።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር -----------------------------

ሌሎች ሰዎችን አይተህ ነበር?

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

አዎን፥ ጥቂት የማውቃቸውን አገልጋዮች፥ ድሮ የሞቱ ሰዎችን፥ በቤታቸው ያገለገልኳቸውን ሰዎችን አይቼ ነበር። እነሱም በወዲያኛው በኩል ነበሩ። እነርሱም *“መምጣት አትችልም፥ መመለስ አለብህ።”* አሉኝ።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር -----------------------------

ወንዞን ብትሻገር ኖሮ መመለስ የማትችል ይመስልህ ነበር? ምንድን ነበር ያንተ ግንዛቤ?

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

እኔ እንደዛ ነበር ያሰብኩት፥ ለዛም ነው ለመሻገር በጣም ስጣጣር የነበረው።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር -----------------------------

አሁን አንዳንድ ህፃናትን ተመልክተህ ነበር፥ ስለልጆቹ እስኪ ንገረን። ይሄኛው በጣም ነክቶኝ ነበር።

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

እንክብካቤ ከሚደረግልኝ ስፍራ የወሰደኝ ያ የሚያምረው ወርቃማው ነገር ጋር እየተወሰድኩኝ ሳለሁ በዚያኛው ስፍራ በኩል ተመለከትኩኝ እናም ህፃናት ልጆች ይሯሯጡ ነበር። እየተጫወቱና ጥሩ ጊዜ እያሳለፉ ነበር። በጣም ቆንጆ ጊዜ እያሳለፉ ስለነበር ከነርሱ ጋር ተቀላቅዬ መጫወት ፈለኩኝ። እዛው ጋር ቆሜ ሳለሁ ነበር የእግዚአብሔርን ድምጽ እንዲህ ሲል የሰማሁት ***"አንተም ከነርሱ ልጆች አንዱ ነህ።"*** እንዲህ በማለት ሳስብ ነበር *"አዎ።"* ልክ እዚህ እንዳሉ ልጆች በ3 የተለያዩ ቡድን ተከፍለው ነበር ሲጫወቱ የነበረው። እናም እግዚአብሔር አንደኛው ቡድን በጦርነት፣ በአደጋ፣ በካንሰር የሞቱ ህፃናት መሆናቸውን ነገረኝ። እንደምታስበው ሁሉም የተለያዩ ቀለማት (አገራት) ናቸው። እየሮጡና እየተጫወቱ የነበሩ ሌላ ቡድን ነበር እናም እርሱ ***"እዛ ጋር ያለው ቡድን የተጨናገፉና (በውርጃ) ወደ እኔ ተመልሰው የተላኩ ህፃናት ልጆች ናቸው።"*** አለኝ። ማልቀስ እንደጀመረ መስማት እችል ነበር፥ የእኔ ጌታ፥ ልክ በጣም በህመም ውስጥ እንዳለ ድምፁ መቀየር ሲጀምር ይሰማኝ ነበር።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር -----------------------------

እርሱ እነዛን ህፃናት ወደ ህዝቡ ላከ፣ እናም ህዝቡ መልሶ እነርሱን ወደ እርሱ ላካቸው።

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

ነገር ግን ሌላም ቡድን በመጫወት ላይ ነበሩ። እርሱም እኚህን የህፃናት ቡድን የዓለምን መንገድ የሚሰሙ የ'ቤተ ክርስትያን' ሰዎች ለሚባሉ (ነን ለሚሉ) እንደላካቸውና እነርሱም በሚስጥር ሄደው ጽንሱን አጨናግፈው ለእርሱ መልሰው እንደላኩለት ነገረኝ።




--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር -----------------------------

አ፣ አምላኬ። ስለዚህ ህፃናቶቹን በነበረው ሁኔታ በቡድን አስቀምጦአቸዋል። እግዚአብሔር አንተ ለቤተ ክርስትያን 2 ማስጠንቀቂያዎችን ይዘህ እንድትሄድ እንደላከህ አካፍለኸኝ ነበር። ሰዎች ሁላችሁም በጥንቃቄ እንድትሰሙ እፈልጋለሁ ምክንያቱም ይህ ሰው በትክክል በጌታ ህልውና ውስጥ የነበረ ሰው ነው። በቅባቱ ብቻ ሳይሆን በህልውናው ውስጥ። እግዚአብሔር ስለሰጠህ ስለ ሁለቱ ማስጠንቀቂያዎች ንገረን።

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

በመጀመርያው ማስጠንቀቅያ እንዲህ አለ ***ሕዝቤ ንስሐ እንዲገቡ ንገራቸው!*** እንዲህ አለ ***እኔን በቁም ነገር እየወሰዱኝ አይደለም።*** በሌላ ማስጠንቀቂያ እኔ ኃጢአት እንደሰራሁ ነገር በጣም ብዙ ህዝብ በእኔ ላይ ቂም ይዟል አለኝ። የሚፈልጉትን ነገር በፈለጉበት ሰዓት ስላልሰጠኋቸው በቤተ ክርስትያን ውስጥ እኔን ይቅር ያላሉ ሰዎች አሉ። ወይም ደግሞ አገልግሎታቸውን ልክ እንደ ሌላ የተለየ አገልግሎት በፍጥነት ስላልባረኩኝ ነው። ወይም አንድ እነርሱ የጸለዩለት ሰው ስለሞተ ይሆናል። በልባቸው በእኔ ላይ ቂም ይዘዋል። ይቅር እስኪሉኝ ድረስ ወደ ፊት እንዲራመዱ አልባርካቸውም።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ------------------------------

ከአመታት በፊት “እግዚአብሔርን ይቅር ማለት (Forgiving God)” በሚል መልእክት ሰብኬ ነበረ እናም አንተ ከርሱ ጋር በተያያዘ ስታጫውተኝ በሚገባ ነው ያስደነቀኝ። ምክንያቱም እግዚአብሔር እያለ የነበረው፥ ሰዎች ይጸልያሉ ነገር ግን የሚፈልጉትን ነገር በፈለጉት ሰዓትና በፈለጉት ሁኔታ አልሰጣቸውም። ስለዚህ በእኔ ይናደዳሉ። እናም እግዚአብሔር ***“እኔ ኃጢአት አልሠራም”*** ብሎ ነገረህ። እኔ ኃጢአት እንደሠራሁ ቆጥረው እየከሰሱኝ ነው። ወደ ውስጥ ለመግባት ሰዎች በእርሱ ላይ የያዙትን ነገር ሁሉ መልቀቅ እንዳለባቸው ነገረህ፤ እግዚአብሔርን ይቅር ማለትና *“እግዚአብሔር ሆይ፥ ሰላንተ እንደዛ በማሰቤ ይቅር በለኝ”* በማለት የያዙትን ነገር ሁሉ መርሳት አለባቸው።

ሁለተኛው ማስጠንቀቅያ ደግሞ በጣም ስሜትን የሚያጭር ጉዳይ ነው፥ ስለ አገልግሎት ነው። ይሄ ማስጠንቀቅያ የተሰጠው በገነት ነው፥ በጸሎት ወቅት አይደለም። በአዕምሮ አኑኢሪዝም በሽታ ምክንያት ወደ ሐኪም ቤት መጥቶ ከአካሉ ወጥቶ ነው፥ በትክክል ከአካሉ ወጥቶ ነው። ነፍስና መንፈሱ ወደ ገነት ሄደው ነበር። ሞቼአለሁ ብሎ አስቦ ነበር፥ በወንበዴዎች የተገደለውን ልጁን ተመልክቶት ነበር፤ እርሱም በገነት እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ሲናገር እየሰማ ነው ያለው። ቀጥልና ንገረን።

----------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ ---------------------------

እርሱም፥ ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙ ማስጠንቀቅያ አሁንም ማስጠንቀቅያ አሁንም ማስጠንቀቅያ የላኩላቸው፥ እንደፈለጉ እየኖሩ ያሉ አገልጋዮች አሉ። ሚስትና ብዙ የፍቅር ጓደኞች እንዳላቸው ነገረኝ። ንስሐ እንዲገቡ ብዙ ማስጠንቀቅያ እንደሰጣቸው ነገረኝ። ፊቴን ከመፈለግ ይልቅ ብርና ነገሮችን እያሳደዱ ነው። ከማስጠንቀቅያ ሌላ ማስጠንቀቅያ አሁንም ሌላ ማስጠንቀቅያ በተደጋጋሚ ልኬላቸዋለሁ። ንስሐ ለመግባት እንቢ አሉ። በማስጠንቀቅያም ቀጥሎ በሌላ ማስጠንቀቅያም ንስሐ ለመግባት አሻፈረኝ ስላሉ፥ **ብዙዎቹ በመድረካቸው ላይ ይሞታሉ**፤ ከእኔ ሳይሆን ከራሳቸው በሚመነጭና እራሳቸውን በሚያሳዩባት እዛችው ስፍራ ላይ ይሞታሉ።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ------------------------------

አንተ ከተመለስክበት ጊዜ ጅምሮ አሁን ከገለጽከው ጋር የሚገጥም ማንኛውንም ነገር ተከስቶ አይተሃል?

----------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ ---------------------------

አዎ፥ በተለየ የማውቃቸው ከተገለጸው ነገር ጋር የሚገጥም አንድ ሁለት የሚሆኑ ሰዎችን አይቻለሁ። በትክክል እየኖሩ አልነበረም፥ በጣም የግብዝ ሕይወት፥ በጣም መጥፎ በሆነ የአኗኗር መንገድን የሚመሩ፥ ነገር ግን እራሳቸውን የወንጌል አገልጋይ ነን ብለው የሚያውጁ ነበሩ፤ በራሳቸው መድረክ ላይ ሞቱ። ሁለቱም የሰላሣ ዘጠኝ አመት ዕድሜ ነበራቸው።

--------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ------------------------------

በእውነት! ይህ ማለት ግን ሁሉም በመድረክ ላይ ወይም ከሰበከ በኋላ የሚሞተው በእግዚአብሔር እየተገደለ ነው ማለት አይደለም። ግን እግዚአብሔር ንስሐ እንዲገቡ ከማስጠንቀቅያም ማስጠንቀቅያ ሰጥቷል።

ለእኔ ያካፈልከኝ ሌላው ነገር ደግሞ ንስሐ የማይገቡ ከሆነ ስለ አሸባሪዎች ታላቅ ጥቃት አሜሪካን እንድታስጠነቅቃቸው እግዚአብሔር የተናገረህን ነበር።

የሚገርመው አንተ የማታውቀው ነገር ቢኖር፥ ስልክ ተደወለልኝ እናም አንድ እውነተኛ ነቢይ ነው ብለው የሚወስዱት አውስትራሊያዊ ሰው አለ። ኢየሱስ ተገለጠለትና እንዲህ አለው ፥ ROE vs WADE (ለሴቶች ፅንስ የማስወረድ መብትን የሚሰጥ ሕግ ነው) የሚባለው በአሜሪካን ካልተገለበጠ፤ እነርሱም ተመልሰው እኔ የምልክላቸውን ህፃናት ልጆችን መከላከል (መጠበቅ) የማይጀምሩ ከሆነ፥ **ከባድና ኃይለኛ** ፍርድ መላ ዩናይትድ ስቴትስን (United States)፥ ሰዎች ወደ ፊት እስከማያውቋት ድረስ እንደሚመታት ነገረው። አንተ ስላየኸው ነገር እስኪ በደንብ ንገረኝ።

--------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

በዚህች አገር (USA) ላይ ጥፋት እየመጣ እንደሆነ ነገረኝ። ሊመታት ያለ ትልቅ ሞገድ አሳየኝ። ይሄ የሆነው በታህሳስ 2004 (እ.ኤ.አ) ከካትሪና (Katrina) በፊት ነበር።

-------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ----------------------------

እግዚአብሔር ይሄ ሁሉ ከመከሰቱ በፊት አሳይቶት ነበር።

--------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ --------------------------

እዚሁ አገር ውስጥ አስቀድመው የገቡ አሸባሪዎችን አሳየኝ።

-------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ----------------------------

እንዳየሃቸው ተናግረህ ነበር ቢሆንም ፊታቸውን ማየት አልቻልክም ነበር፥ ነገር ግን አንድ ሴትና አራት ወንዶች ለሆነ ቡድን ሲሰሩ ነበር። ከፍተኛ ጥቃት ነው። እያወራን ያለነው ትልቅ ስለሆነና ሰዎች በቀላሉ ሊቀበሉት ስለማይችሉት ነገር ነው። በጣም ትልቅ ጥፋት።

ባሳለፍነው ሳምንት በዚህ ዝግጅት ላይ ወንድም ካርተርና (Brother Carter) ወንድም ቶሚ ቤትስ (Brother Tommy Bates) ስለ ካርተር ሚስት የ21 ደቂቃ ሞትና፥ 40 አመት ወደ ኋላ ተመልሳ በመኪና አደጋ የተገደለውን ልጇን ማየቷን ሲናገሩ ነበር።

ጳጳስ ኬሊ በአዕምሮ አኑኢሪዝም በሽታ ምክንያት በሐኪም ቤት ውስጥ ሳለ አንድ ነፍስ ሲመጣ አየና አንስቶት ወዲያውኑ ወደ እግዚአብሔር ህልውና ሲወስደው ተመልክቷል።

አሁን እናንተ አድማጮች (አንባብያን) *"ይሄ ሁሉ ነገር ስለምንድን ነው?"* ብላችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ። በሁለተኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ላይ ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ እንደተነጠቀ፥ ወደ ገነትም እንደ ተነጠቀ ይናገራል። በዚያም ሰው እንዲናገረው ያልተፈቀደለትን ነገር ሰምቷል። ጳውሎስ ተመልሶ መጥቶ ያየውን ነገር ቢነግረን ልናምነው እንደማንችል ተናግሯል። ሰዎች ሊያምኑ አይችሉምና።

1ኛ ቆሮንቶስ 2:9 *"ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው"*

ነገር ግን እግዚአብሔር በመንፈሱ፣ መሰረታችን በሆነው በእግዚአብሔር ቃልና እንደዚህ ዓይነት ነገር በገጠማቸው ሰዎች ማስተዋል ይህን ነገር ገልጦአል።

በቴኔሲ (Tennessee) ባለችው ቻታኑጋ (Chattanooga) ከተማ ዶ/ር ሞሪስ ኤስ. ሮውሊንግስ (Dr. Maurice S. Rawlings) የሚባል ሐኪም እንዳለ ታውቃላችሁ፤ ከሞት በኋል ስላለ ሕይወት ብዙ መጽሐፍቶችን ጽፏል። ወደ ሲዖል የሄዱ ሰዎችን አንቅቶአቸዋል፥ ከአካላቸው ተለይተው ወደ ገነት የሄዱ ሰዎችን አንቅቶአል። ይሄ ነገር በእርሱ ላይ መሆን ሲጀምር አማኝ አልነበረም። ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ የማይናገሩ ሐኪሞች አሉ። በቀዶ ጥገና ጊዜ ከአካላቸው ተለይተው የወጡ ሰዎችን አነጋግረዋል፥ ከአካላቸው ተለይተው የወጡት አደጋ ከደረሰባቸው በኋላ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እናንተ አካልም፣ ነፍስም፣ መንፈስም ናችሁ ይላል። አንዳንድ ሰዎች የነፍስ እንቅልፍ (soul sleep) በሚባለው እንደሚያምኑ አውቃለሁ። ነፍስና መንፈስ እዛው በአካል ውስጥ ይቀራሉ ብለው ያምናሉ። የንስሐ ቦታ እንዳለና እርሱም ሰዎች በሆነ እሳት መካከል ያልፋሉ ከዚያም ይነፃሉ ከዚያም ተመልሰው ይወጣሉ ብለው የሚያምኑ ሌሎች ሰዎችንም አውቃለሁ። ሰዎች ስለገነት ስላላቸው ብዙ ጥያቄዎች ተከታታይ ዝግጅት እንዳዘጋጅ ያደረገኝ ጌታ ነው።

ነገር ግን ጳጳስ፥ በቦታው ተገኝተህ ያን ሁሉ ነገር ማየትህ፥ በሕይወት ላይ ወይም ደግሞ ወደ ፊት ባለው አጠቃላይ ነገር ላይ ያለህን አይታ ቀይሮብሃል?

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ ---------------------------

አሀ፥ አዎን! እግዚአብሔር ሰዎች ይህን ነገር **በቁም ነገር እንዲወስዱት** እንድነግራቸው ተናግሮአል። ይህን ነገር እንደሚገባው በቁም ነገር እየወሰዱት አይደለም፥ ምንም ዴንታ አይሰጣቸውም።

እናም ድንበሬ ውስጥ መሆኔን ለማረጋገጥ በየእለቱ በራሴ ላይ በዝርዝር እሠራለሁኝ። ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን እንጂ ወደ ግራ በጣም ርቀህ አትሂድ። በእጆቼና በጉልበቴ ሆኜ ወደ እግዚአብሔር እጮሃለሁ። በእግዚአብሔር ፊት ሄጄ *"እግዚአብሔር ሆይ፥ በእኔ እንድትጠቀም እፈልጋለሁ ምክንያቱም እዛ ምን እንዳለ አውቃለሁ።"* እላለሁ። ደግሞም ነፍሳትን ለዘላለም በጣም ከመርፈዱ በፊት ማስጠንቀቅ አለብኝ። እናም የምሰራው ይሄን ነው።

-------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ------------------------------

የገነት ወርቃማ መርከብ (Heaven Golden Vessel) የሚል መጽሐፍ አለ፥ የእርሱ ምስክርነት ነው። (Amazon.com ላይ ፈልጉት) አንተ እዚህ መቀመጥህ ራሱ ተአምር ነው ምክንያቱም ስለአንዩሪዝም ብዙ ነገር ስለሰማሁ ነው። ሐኪሞቹ እራሳቸው ተናደህ ግንባርህን ብትቋጥር እንኳን እንደምትሞት ነግረውህ ነበር።

---------------------------- ጳጳስ ኧርዝኩኤክ ኬሊ ---------------------------

ባለቤቴ ግንባሬ ላይ እጇን ጭና እንዲህ አለች "እንዳትቋጠር፥ ብትቋጠር ትሞታለህ።" እነርሱም እዛው እሞታለሁ ብለው ነበር ያሰቡት።

-------------------------- አቅራቢ ፔሪ ስቶን ጁኒየር ------------------------------

ሞቷል ለተባለ ሰው በጣም ጥሩ ነገር እየሠራህ ነው። *"ይሄን ሰው ማናገር አለብህ"* ብሎ የነገረኝ ጓደኛ አለኝ። በካሊፎርንያ (California) ሳገኝህ ወዲያውኑ ነበር ለምስክርነትህ ምስክር የሆንኩት።

ይህን ነገር የማያምኑ ሰዎች እንዳሉ አውቃለሁ፥ እንደዚህ ያሉ ገጠመኞች እውነት ሊሆኑ አይችሉም ብለው ያምናሉ። አይደለም ሰዎች ስሙኝ፥ ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ነገር ሲኖራችሁ ታውቃላችሁ። ታውቁታላችሁ። ጳጳስ ከኔ ጋር እዚህ መሆንህ ታላቅ አክብሮት ይሰጠኛል።

---

Website: www.EarthquakeKelleyMinistries.org

E-mail: eqkelly@msn.com

**በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ ጌታ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።**

*ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ቢኒያም ጌታቸው*
Translated to Amharic by Biniyam Getachew, bgmanoftheyear@gmail.com